# <u>የሀገሬን መሬት ሙጃ በቀለበት፤</u>

የሀገሬን መሬት ሙጃ በቀለበት የሚያበቅለውን ስንዴ
የኢትዮጵያን መሬት አሽክት በቀለበት የሚያበቅለውን ስንዴ
ገበሬውም ተሰዷል በአልቪን እያጨደ የሚያርሰው በጓንዴ።

    በሳይንስ ምርምር በተክኖሎጂ እድገት
    አረም ይጠፋል ይሉናል ሳይንስ የተማሩት
    ነቅሎ የሚያወጣው ማረሻና ዶማ ሳይጨመርበት።

እንኳንስ ሀገር ዳር ይዞ እስከ ዳር ያወቀው ዓለም
እንዲህ በቀላሉ ይጠፋል ይሉናል ስር የሰደደ አረም።

    ሀገሬን ኢትዮጵያ አረም ከዋጣት
    ይህው ሊሞላነው ሃያ አራት ዓመት።

የሚለምድ መስሎአቸው ጎተው አስገብተው የበረሃ ዝንጀሮ
ቡቃያውን ፈጀው ያለውን ከጓሮ።

    የሚያባረው ጠፋ ሁሉም ተዘባራ
    እየዞረ በላው አንድ በአንድ በተራ
    ከቤት የገባውን ሳይቀር ያለውን ከጎተራ።

የአውሮፓ ዝንጀሮ ከሰው ጋር ተላምደው አብረው ይውላሉ፤
የአፍሪቃ ዝንጀሮ ግን ሰውን ባዩ ቁጥ ይበረግጋሉ፤
የአውሬነቱ ጸባይ ስላለቀቃቸው፤
ሰው መናከስ ሆነ የእነሱ ግብራቸው።

    ሀገር ጤና አይገዛም ዝንጀሮ ካልወጣ
    መበላቱ አይቀርም የደረሰው እጣ።

ሁሉም በየአለበት ጥሩንባውን ነፍቶ በሰልፍ ያባርረው
የግንቦቱን ዘር  ሊቃቅሞ እንዳይበላው
አሁን ካልታሰረ በኋላ መዘዙ ብዙ ነው።

ከጫካ የመጣ ምን ግዜም አውሬ ነው

መናከሱ አይቀርም ብሎ እያዛለው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ክንድህን አጠንክር በዩ አለህበቱ

ዝንጀሮ መያዣው ተቃርቦአል ጊዜ አቱ

መፍረክረክ ጀምሮአል የተማመነበት ኃይልና ጉልበቱ

መስኮቱ ተከፍቶአል አንድ አንድ እያለ የሚሾልክበቱ

በሩ ብቻ ቀርቶአል አንዴ ነጉዶ የሚወጣበቱ።

የሚመክት የለም ጭፍራው ተበታትኖአል

በአራቱ መአዘን ሲባዝን አይተናል

ከዚያው ከዋሻው ውስጥ እንዳለ ይያዛል

ደፋር ከተገኘ አጥሩን ሰባብሮ የሚጥል።

ለምድር ነገሥታት መጮህ አቁማችሁ

ይህነው ያነ ነው መባባል ትታችሁ

ሰላምና ፍቅር በአንድ መስርታችሁ

ጸሎት ብታደርጉ በዩ እምነታችሁ

በቀናት ይወጣ ነበረ አውሬው ከቤታችሁ።

ጸሎታችሁ ሁሉ ከሰማይ ይደርሳል

እንባችሁም ሲፈስ ፈጣሪያችሁ ያያል

የንጉሦች ንጉሥ የኃያላን ኃያል

ቀኑን ሳያስረዝም ነገ ዛሬ ሳይል

አውሬውን ለማጥፋት ክንዱን ይዘረጋል።

የኢትዮጵያ አምላክ መቼ ያንቀላፋል

አባትና ልጁን በአንዴ ሲያስተኛቸው አይተናል።

የኢትዮጵያ አምላክ መቼ እርቀ ያውቃል

አላስቀርብ አለ እንጂ የእኛ ኃጢአት ተንኮል።

አንተን እንድንከተል እንደ አባቶቻችን

መንገዳችን ሁሉ በአንተ ብቻ እንዲሆን

መለአከ ላክልን የሚጠብቅ እኛን።

በዚች ቅድስት ሀገር ተስማምተን እንዳንኖር

የሚያለያዩንን ልቦና ስጣቸው ፈጣሪያችን እግዜር።

ኢትዮጵያን ጠብቃት ቸሩ መድኃኔ ዓለም!

ከተናካሽ አውሬ ሀገርን ከሚያወድም

ጣት እየተቀሳሰርን እንዳንኖር ዘላዓለም

ለእኛም አድለን ፍቅርና ሰላም።

ታሕሣሥ፡፳፫ ፪፻፲፯ (01/01/2015)